የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**18[th] Year No. 37**
**ADDIS ABABA 26[th] June 2012**

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፷፭/፪ሺ፬

የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................ገፅ ፮ሺ፫፻፶፪

## CONTENTS

**Regulation No. 265/2012**

Ethiopian Petroleum Supply Enterprise Establishment
Council of Ministers Regulation........................Page 6352

### ሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፭/፪ሺ፬

### የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፭/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 265/2012

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN PETROLEUM SUPPLY ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Petroleum Supply Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 265/2012".

**2. Establishment**

1/ The Ethiopian Petroleum Supply Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**3. Supervising Authority**

A body to be designated by the government shall be the supervising authority of the Enterprise.

**4. Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

**፭. ዓላማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የሀገሪቱን የነዳጅ ፍላጎት በማጥናት የተጣራ የነዳጅ ምርት ወደሀገር በማስገባት እና የነዳጅ ድፍድፍ ወደሀገር አስገብቶ በማጣራት ለነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ማቅረብ፤

፪/ ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን ብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ መጠን ማቀድ፣ ማከማቸት፣ ክምችቱን ማስተዳደር እና ከመንግሥት በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ከክምችት ወጥቶ እንዲከፋፈል ማድረግ፤

፫/ በሀገር ውስጥና እንደአስፈላጊነቱ በጎረቤት ሀገሮች የራሱን የነዳጅ ማከማቻ ዴፖዎች መገንባት እና የነዳጅ ማከማቻ ዴፖዎች አገልግሎት በሚሰጡ ኩባንያዎች ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ፤

፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማከናወን።

**፮. ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፪ ቢሊዮን (ሁለት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፭፻ ሚሊዮን ብር (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

**፯. ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

**፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

**፱. የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፲፱፻፹፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

**፲. ስለብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር መፍረስ**

በአዋጅ ቁጥር ፹፪/፲፱፻፺፱ ተቋቁሞ የነበረው ብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፴፬ መሠረት በዚህ ደንብ ፈርሷል።

**፲፩. የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፲፱፻፹፭ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና በአዋጅ ቁጥር ፹፪/፲፱፻፺፱ ተቋቁሞ የነበረው ብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

**፲፪. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**5. Objectives**

The objectives for which the Enterprise is established are:

1/ on the basis of assessment of the country's demand, to supply petroleum to distribution companies by importing clean products and by importing and processing crude oil;

2/ to forecast, maintain and administer the required national petroleum reserve and, based on instructions of the government, supply petroleum products from the reserve;

3/ to build its own petroleum depots within the country and, as may be necessary, in neighboring countries; and to invest in companies operating petroleum depot facilities;

4/ to engage in any other related activities necessary for the attainment of its objectives.

**6. Capital**

The authorized capital of the Enterprise is Birr 2,000,000,000 (two billion Birr) of which Birr 500,000,000 (five hundred million Birr) is paid up in cash and in kind.

**7. Liability**

The Enterprise may not be held liable beyond its total assets.

**8. Duration**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

**9. Repealed Regulation**

The Ethiopian Petroleum Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 210/1995 is hereby repealed.

**10. Dissolution of the National Petroleum Reserve Depots Administration**

The National Petroleum Reserve Depots Administration established under Proclamation No. 82/1997 is hereby dissolved pursuant to Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

**11. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Ethiopian Petroleum Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 210/1995 and the National Petroleum Reserve Depots Administration established under Proclamation No. 82/1997 are hereby transferred to the Enterprise.

**12. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 26th day of June, 2012.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ